የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፴
አዲስ አበባ– ታህሣሥ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 30
ADDIS ABABA - 5th January 1999

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፻፶/፲፱፻፺፩ ዓ·ም
ለጤና ልማት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ...................................... ገጽ ፱፻፷፪

## CONTENTS

Proclamation No. 150/1998
International Development Association Credit Agreement for financing the Health Sector Development Program support Project Rectification proclamation ...................................... Page 962

## አዋጅ ቁጥር ፻፶/፲፱፻፺፩
## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለምአቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለጤና ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ኤስ·ዲ·አር ፸፭ ሚሊዮን ፻ሺህ (ሰባ አምስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺህ ኤስ·ዲ·አር) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትየጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለምአቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ·ኤ·አ· አክቶበር ፴ ቀን ፲፱፻፺፰ በዋሽንግተን ዲሲ የተፈረመ በመሆኑ፤

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለምአቀፍ ውሎች ተፈጻሚ ከመሆናቸው በፊት መጽደቅ ስላለባቸው፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታኅሣሥ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ·ም· ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፤

በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለጤና ልማት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፻፶/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 150/1999
## A PROCLAMATION TO RATIFY THE DEVELOPMENT CREDIT AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

WHEREAS, a Development Credit Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit amount of SDR 75,100,000 (seventy five million one hundred thousand Special Drawing Rights) for financing the Health Sector Development Program Support Project, was signed in Washington D.C, on the 30th day of October, 1998;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 5th day of January, 1999;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Credit Agreement for financing the Health Sector Development Program support Project Ratification Proclamation No. 150/1999."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለምአቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ·ኤ·አ· አክቶበር ፴ ቀን ፲፱፻፺፰ በዋሽንግተን ዲሲ· የተፈ ረመው ቁጥር ፫ሺ፩፻፵ ኢ·ት· የብድር ስምምነት ነው።

፫· <u>የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ኤስ·ዲ·አር· ፸፭ ሚሊዮን ፩፻ሺ(ሰባ አምስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺህ ኤስ·ዲ·አር) በብድር ስምምነቱ በተመ ለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከታህሣሥ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ታህሣሥ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Credit Agreement" means the Credit Agreement NO. 3140 ET, signed in Washington DC, on the 30th day of October, 1998, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association.

3. *Power of the Minster of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilisation of the credit amount of SDR 75,100,000 (seventy five million one hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Credit Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 5th day of January, 1999.

Done at Addis Ababa, this 5th day of January, 1999.

NAGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE